24 ግንቦት 2014

4/1570/14

በአባሪው ለተዘረዘሩት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የጫት ምርት የውጭ ሽያጭ ውል ምዝገባ አፈጻጸምና አተገባበር ይመለከታል</u>፤

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በቁጥር 1/.1.30/32138 ግንቦት 22 ቀን 2014 በተጻፈ ደብዳቤ የጫት ምርት የውጭ ንግድ ፍትሃዊ እና እኩል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እንዲሁም ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ የጫት ምርት በውል ምዝገባ እና አስተዳደር አሰራር ስርዓት ውስጥ ማካተት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ማንኛውም (እርጥብ እና ደረቅ) የጫት ምርት ሽያጭ ውል ምዝገባና ማረጋገጫ እንዲሁም የመሳኪያ ፍቃድ አገልግሎት ከግንቦት 20 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን በመግለጽ ለባንኮች የጫት ምርት የውጪ ንግድ ውል (Export Contract) ኤክስፖርት ጥያቄ ሲቀርብ በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የጫት ምርት ውል ምዝገባ ማረጋገጫ የተሰጠውና የፀደቀ መሆኑ እየተረጋገጠ እንደሚገባውና የምዝገባ ማረጋገጫ ያልተሰጠው እና ለባንኮች ማቅረብ ያልቻለ ላኪ ኤክስፖርት ፐርሚት እንዳይሰጠው፤ በተጨማሪም ጉምሩክ ኮሚሽን ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የይለፍ የጫት ምርት የመሳኪያ ፈቃድ የተሰጠው መሆኑን በማረጋገጥ ተግባራዊ እንዲደረግ አሳስቧል፡፡

በመሆኑም በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በኩል የጫት ምርት የመሳኪያ ፈቃድ አገልግሎት ከግንቦት 20 ቀን 2014 ጀምሮ የሚሰጥ በመሆኑ ማንኛውም የጫት ምርት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የይለፍ የጫት ምርት የመሳኪያ ፈቃድ የተሰጠው ስለመሆኑ በጥብቅ ጥንቃቄ እየተረጋገጠ የጉምሩክ አገልግሎት እንዲሰጥ እያሳሰብኩ፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የላከውን "በወጪ ምርቶች ውል ምዝገባ እና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 21/2012 መሠረት የጫት ምርት የውጪ ውል አፈጻጸም እና አሰራር ስርዓት" 07 ገጽ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ

የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ</u>፤

- ለኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለአምራችና ወጪ ንግድ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለአቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለኮሙኒኬሽን የስራ ሂደት

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሀዋሳ ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዋሽ ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ገ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

በያሉበት፡

No.2
Ethiopian Customs Commission
Records & Documentation

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic Of Ethiopia
Ministry Of Trade & Regional Integration

ቀን /Date 2 2 ግንቦት 2014

ቁጥር/No 011/30/32138

ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

ለኢፌዴሪ ጉምሩክ ኮሚሽን

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የጫት ምርት የወጪ ሽያጭ ውል ምዝገባ አፈፃፀምና አተገባበር ስለማሳወቅ

ሀገራችን ለውጭ ገበያ ከምታቀርባቸው ዋና ዋና የግብርና ምርቶች አንዱ የጫት ምርት ሲሆን ከዘርፉ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ ገቢ ግኝት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ቢሆንም በጫት ምርት የላኪነት የንግድ ስራ ፈቃድ አተገባበር፣ በጫት ምርት ውል አገባብና አፈፃፀም፣ በመላኪያ ፈቃድ አሰጣጥ እና በጫት ምርት የወጪ ምንዛሬ ክፍያ አፈፃፀም ችግሮች የሚታዩበት በመሆኑ ከዘርፉ መገኘት የሚገባው ገቢ ጥቅም እያሳጣ ይገኛል።

በመሆኑም የጫት ምርት የወጪ ንግድ ፍትሃዊ እና እኩል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እንዲሁም ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ የጫት ምርት በዉል ምዝገባ እና አስተዳደር አሰራር ስርዓት ውስጥ ማካተት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ስለሆነም ማንኛውም (እርጥብና ደረቅ) የጫት ምርት ሽያጭ ውል ምዝገባና ማረጋገጫ እንዲሁም የመላኪያ ፍቃድ አገልግሎት ከግንቦት 20 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የምናደርግ መሆኑን እየገለፅን ለባንኮች የጫት ምርት የወጪ ንግድ ውል (Export contract) ኤክስፖርት ጥያቄ ሲቀርብ በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚ/ር የጫት ምርት ውል ምዝገባ ማረጋገጫ የተሰጠውና የፀደቀ መሆኑ እየተረጋገጠ እንደሚገባውና የምዝገባ ማረጋገጫ ያልተሰጠው እና ለባንኮች ማቅረብ ያልቻለ ላኪ ኤክስፖርት ፐርሚት እንዳይሰጠው እያሳወቅን በተጨማሪም ጉምሩክ ኮሚሽን ከሚኒስቴር መ/ቤታችን የደለፍ የጫት ምርት የመላኪያ ፈቃድ የተሰጠው መሆኑን በማረጋገጥ ተግባራዊ እንዲያደርግ እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር

ካሣሁን ጎፌ ባሰማ
ሚኒስትር ዴኤታ

እንዲያውቁት፡-

- ለክቡር ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር

ግልባጭ፡-

- ለጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት
- ለድሬደዋ ወጪ ንግድ ቅ/ጽ/ቤት
- አባሪ የጫት ምርት የሽያጭ ውል እና የአተገባበር ስርዓት ሰነድ 5 ገፅ

Tel. +251-5-527676
Fax. +251-5-501697
P.o.Box: 704
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

# KHAT EXPORT SALES CONTRACT

CONTRACT No. ___________

Date: ____________

Contracting Parties:

This Contract is made and entered on the _______ day of _______ by and between _____________________, Address: _____ city, ______ Sub-city, Woreda ____, House No. _______, Tel. __________________ (Hereinafter called the "**Exporter/Seller**") and

_____________________, Address: ______________________________ (Hereinafter called the "**Buyer**") for the sale of __________________.

The Parties Agree as follows:

1. The Seller agrees to sell and the buyer agrees to buy ________________ (Eg. Ethiopian Origin Khat ) as per the under mentioned terms and conditions:

   Commodity: __________________________ Origin ______________________
   Specification: ________________________________________________
   Quantity: __________________________ Unit Price ____________________
   Packing: __________________________

2. Port/Place of Loading: ______________________________________
3. Port/Place of Discharge: ____________________________________
4. Terms of Payment: _________________________________________
5. INCOTERM: _______________________________________________
6. Shipment Period: __________________________________________
7. Governing Law: ___________________________________________
8. Dispute Settlement Mechanism: : ___________________________

The Parties or duly authorized Representatives of the Parties hereto have subscribed their names and signature as of the date above, and executed this Contract in ______ counterparts (copies).

| For and Behalf of the Seller | For and Behalf of the Buyer |
|---|---|
| ______________________________ | ______________________________ |
| (Signature of Authorized Representative and Stamp of Company) | (Signature of Authorized Representative and Stamp of Company) |

Note: This format is a template for reference purpose only to guide the registration of Export Contracts. Contracting Parties are free to include additional terms and conditions.

Ethiopian Customs Commission Records & Documentation
ETC 2 No.2
Ministry Of Trade and Regional Integration Archives

# የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

# Ministry of Trade and Regional Integration

[illegible] የወጪ ምርቶች ውል ምዝገባ እና አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 21/2012
[illegible] መሰረት የ[illegible] ምርት የወጪ ውል አፈጻጸም እና አሰራር ስርዓት

ግንቦት 2014

ቁጥር 2
No.2
Ethiopian Customs Commission
Records & Documentation
የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade and Regional Integration
Archive
መዝገብ ቤት

# የጫት ምርት የወጪ ዉል አፈፃጸምና አሰራር

የወጪ ምርቶች ንግድ ዉል የመፈፀመዉ ሃላፊነት እና ተጣቂነት ያለዉ የጫት ዉል ምዝገባ አፈጻጸም ስርዓት በመዘርጋት የጫት ምርትን የወጪ ገበያ አሰራር ስርዓት ማሻሻል አስፍላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነዉ።

አላግባብ የጫት ምርት የወጪ ምንዛሪ ገቢ ሳስገኝ በህግ ወጥ አሰራር ጥሰት ምክንያት የሚባክነዉን ምርት በመከላከ ከዘርፉ የሚገኘዉን የወጪ ምንዛሪ ገቢ ማሻሻል በማስፈለጉ ነዉ፡

የጫት ምርትን የወጪንግድ ፍትሃዊ እና ንግዱን ማህበረሰብ እኩል ጠተቃሚነትን ለማረጋገጥ ከባለድርሻ አካለት ጋር ተቀናጅቶ በመስራት ሀገራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ በማስፈለጉ ነዉ።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ አስፈፃሚ አካላት ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 21 የንግድና ቀጣናዊ ትስሰር ሚኒስቴር ባወጣዉ የወጪ ምርቶች የዉል ምዝገባ አፈፃጸም መመሪያ ቁጥር 21/2012 መሰረት የጫት ምርትን በዚህ መመሪያ ዉስጥ በማካተት ተግባራዊ ለማድረግ ነዉ።

Ethiopian Customs Commission
Records & Documentation
No.2
Ministry Of Trade and Regional Integration Archives

## አንቀፅ አንድ

## ጠቅላላ

1. አላማ፣ የጫት ምርት ወጪ ንግድ ህግ ወጥ የአሰራር ጥሰቶችን በመከላከል ከዘርፉ የሚገኘዉን የወጪ ምንዛሪ ገቢ ማሳደግ ነዉ።
2. የጫት ምርት ወጪ ዉል ማለት በወጪ ምርቶች ላይ በላኪዎች (ሻጭ) እና በወጭ ሀገር በሚገኙ ገዢዎች መካከል የሚፈጸም ዉል ነዉ።
3. የጫት ምርት ወጪ ዉል ምዝገባ፣ ማለት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣን በተሰጠዉ አካል የሚከናወን በሀገራችን ላኪዎች (ሻጭ) እና በዉጭ ሀገር በሚገኙ ገዢዎች መካከል የሚፈጸም ዉል መስፈርችን ማሟላቱን በማረጋገጥ የሚደረግ ምዝገባ እና የሚሰጥ የምዝገባ ማረጋገጫ ነዉ።

## አንቀፅ ሁለት

### የጫት ምርት ዉል ስለመመዝገብ፤ የምዝገባ ዉጤት እና የመላኪያ ፍቃድ ስለመስጠት

4. የጫት ምርት የሽያጭ ዉል አመዘጋገብ የአሰራር ስርዓት

4.1 የዉል ሽያጭ ዋጋ በተመነዉ መዳረሻ ገበያዎች ተመን መሰረት፣ ክፍያዉ ሙሉ በሙሉ፣ የሽያጭ ዉል ከአንድ ወር ባላይ ያለሆነዉ፣ ምርቱ የሚጫንበት የትራንስፖርት አይነት እና ሌሎች መስፈርቶች መሟላታቸዉን በማረጋገጥ መመዝገብ እና የምዝገባ ማረጋገጫ መስጠት።

4.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተመዘገበዉ እና በተሰጠዉ የምዝገባ ማረጋገጫ ላይ የጫት ምርት ልዩ ምዝገባ ቁጥር በመስጠት እና የመሚኒስቴር መ/ቤቱን ማህተብ በመምታት ዉሉን ማፅደቅ።



Ethiopian Customs Commission Records & Documentation
ቁጥር 2 No.2
Ministry Of Trade and Regional Integration Archives
መዝገብ ቤት

4.3 የተመዘገብ የጫት የሽያጭ ዉል ለባንክ በማቅረብ በመላክ ሂደት የሚጠየቁ የባንክ የመላኪያ ፍቃድ እና የጉሙሩክ መስፈርችን አሟልቶ ምርቱን ወደ ዉጪ ለመላክ ያስችለዋል እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገበ የጫት ምርት የወጪ ንግድ ሽያጭ ዉል ምርትን ወሰ ዉጪ ለመላክ አይስችለዉም ዉጤትም አይኖረዉም፡፡

4.4 የጫት የመላኪ ፍቃድ በገባዉ ዉል የጊዜ ገደቡ ያላለፈበት፤ የሽያጭ ዉሉ መሰረት መጠኑን በትክከል የሚገልፅ፤ የባንክ የመላኪያ ፍቃድ፣ በገዢዉ በኩል ወጪ ምንዛሪ ክፍያ የተፈፀመበት ኢንቮይስ አሟልቶ ሲቀርብ የጫት ምርት የመላኪያ ፍቃድ አገልግሎት ይሰጠዋል፡፡

## አንቀፅ ሶስት

## ኃላፊነት እና ተግባር

### 5. ንግድና ቀጣናዊ ሚኒስቴር

5.1 የጫት ምርት የወጪ ሽያጭ ዉልን ምዝገባን ያከናዉናል፤ አፈጻፀሙን ይከታተላል

5.2 የጫት ምርት የመላኪያ ፍቃድ ይሰጣል ወይም ያከናዉናል፤ አፈጻፀሙን ይከታተላል

5.3 የጫት ምርት የመላኪያ የዋጋ ተመነ በታች አሳንሶ በሚሸጡ፤ የወጪ ምንዛሪ ክፍያ ከተፈጸመበት የጫት ምርት መጠን በላይ አስበልጠዉ በሚልኩ አካላት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

### 6. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ እና ንግድ ባንኮች

6.1 በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የተመዘገበዉን እና የጸደቀዉን የጫት ምርት የሽያጭ ዉል መሆኑን በማረጋገጥ ይመዘግባል እንዲሁም የመላኪያ ፍቃድ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

Ethiopian Customs Commission Records & Documentation
No.2
Ministry Of Trade and Regional Integration Archives

6.2 ለጫት ምርት ሽያጭ አላማ ወደ ባንክ የገባ የወጪ ምንዛሪ የክፍያ ኢንቮይስ ማረጋገጫ ሰነድ ይሰጣል፡፡

**7. የኢትዮጵያ ጉሙሩክ ኮሚሽን**

7.1 የጫት ምርት ዉል እና መላኪያ ፍቃድን ሰነዶች በማረጋገጥ ክሊራንስ ይሰጣል.

7.2 የጫት ምርት ሽያጭ ከተሰጠዉ የመላኪያ ፍቃድ ላይ ካለዉ ምርት መጠን እና ክፍያ በላይ አለመሆኑን በማረጋገጥ አገልግሎት ይሰጣል፤

**8. የጫት ምርት ላኪዎች**

8.1 የጫት ሽያጭ ዉል ማስመዝገብ እንዲሁም የመላኪያ ፍቃድ በመያዝ ምርትን የመላክ ግዴታ

8.2 መልካም የዉል አፈጻጸም ገጽታ የመገንባት እና በመልካም ንግድ ስነምግባር የመስራት ግዴታ

8.3 ከሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መስራት

8.4 የወጡ የጫት የግብይት ህግ ማዕቀፎችን ማክበር

## እንቀፅ አራት

**9. አስተዳደራዊ እርምጃ**

በጫት ምርት የወጪ ንግድ ግብይት ዉል ህገ ወጥ ድርጊት እና የአሰራር ጥሰት የሚፈጽሙ ወይም የሚተላለፉ የግብይት ተዋናይ ላይ በዉጪ ንግድ ዉል ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 21/2012 አንቀፅ 20 መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

Ethiopian Customs Commission
Records & Documentation
No.2
Ministry Of Trade and Regional Integration Archives
መዝገብ ቤት